# መልክዐ ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ካልእ (ዘአኀተሞ ገብረ ሥላሴ)

| መልክዐ አእላፍ መላእክት ካልእ-ግዕዝ | የቅዱሳን አእላፍ መላእክት 2ኛ መልክዕ በአማርኛ |
| --- | --- |
| ፩. ሰላም ለዝክረ ስምክሙ ዘኢይትከሀል ለተነግሮ፤ እንበለ ዳዕሙ አንክሮ፤ ትጉሃን አእላፍ እለ ትጽሕቁ ለዘምሮ፤ ለቅሑኒ ንዋየ ጽድቅ ዘዚአክሙ አእምሮ፤ ዜና ውዳሴክሙ እንግር ወእክሥት ምሥጢሮ፡፡ | 1. ለዝክረ ስምክሙ፡- ከማድነቅ ብቻ በቀር ሊነገር ለማይቻለው ስም አጠራራችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ለማመስገን የምትተጉ ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ሆይ! የውዳሴያችሁን ዜና እነግር ዘንድ ምሥጢሩንም እገልጥ ዘንድ የእናንተን የጽድቅ ገንዘብ ዕውቀትን አበድሩኝ፡፡ |
| ፪. ሰላም ለሥዕርተክሙ ዘኢይትዐወቅ ኍላቄሁ፤ ለርእስክሙኒ ዘአክሊለ ብርሃን ሥርጋዌሁ፤ አመ በጽሐኒ ምንዳቤ ለኢዮብ ሐዋርያሁ፤ ረዱ እምሰማያት ለናዝዞትየ ናሁ፤ ለንጉሠ ስብሐት ዐቢይ አእላፍ ሐራሁ፡፡ | 2. ለሥዕርተክሙ፡- ቍጥሩ ለማይታወቅ ጠጉራችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ማጌጫው የብርሃን አክሊል ለሆነ ራሳችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ከፍ ከፍ ያለ የክብር ንጉሥ ወታደሮች ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ሆይ! የኢዮብ መልእክተኛ ችግር በደረሰብኝ ጊዜ እነሆ እኔን ለማረጋጋት ከሰማያት ውረዱ፡፡ |
| ፫. ሰላም ለገጽክሙ ዘለዓለም ፍሡሕ፤ ለቀራንብቲክሙኒ ምጽላላተ ዐይን ብሩህ፤ ከዋክብተ ሰማይ አእላፍ መገብተ አውራኅ፤ ቤዛ ይኩነኒ ምሕረትክሙ በቅድመ ፈታሒ መሢሕ፤ ለዘይደልወኒ ተኰንኖ ወመዊት በፍትሕ፡፡ | 3. ለገጽክሙ፡- ለዘለዓለሙ ደስተኛ ለሆነው ፊታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የብሩህ ዐይን መጋረጃ ለሆነው ቅንድባችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ወሮችን የምትመግቡ የሰማይ ከዋክብት ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ሆይ! በፍርድ ሞትና ኵነኔ ለሚገባኝ ለእኔ ፈራጅ ለሆነው አምላክ ምልጃችሁ ቤዛ ይሁነኝ፡፡ |
| ፬. ሰላም ለአዕይንቲክሙ አዕይንተ ርግብ ብሩሃን፤ ለአእዛኒክሙኒ እለ ያፀምዓ ቃለ ቀርን፤ ኢይርከበኒ ጸናሒ እከየ ሳምን ዘመን፤ ጽንሑኒ ውስተ ሠናይ ለገብርክሙ ምእመን፤ አእላፍ አጋዕዝትየ መላእክት ኄራን፡፡ | 4. ለአዕይንቲክሙ፡- እንደ ርግብ ዐይኖች ብሩሃን ለሆኑ ዐይኖቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የከበሮ ድምፅ ለሚያደምጡ ጆሮዎቻችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ቸሮች ጌቶቼ ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ሆይ! የስምንተኛውን ክፋት የሚጠብቅ እናዳያገኘኝ የማምን እኔን ባሪያችሁን በበጎ ቦታ ጠብቁኝ፡፡ |
| ፭. ሰላም ለመላትሒክሙ እለ ከመ ሮማን አቅየሐይሐ፤ ለአእናፊክሙኒ ዘተመሰሉ ጽንሐሐ፤ እስመ እምኍንዱይ መዋዕል ጸናሕኩክሙ ጸኒሐ፤ ከመ ይጸንሕ መኰንን ዘያሌዕሎ መሢሐ ሐውፁኒ አእላፍ ወበሉኒ በሐ፡፡ | 5. ለመላትሒክሙ፡- እንደ ሮማን ለሚያቅላላ ፊታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ጽንሐ ለመሰሉ አፍንጫዎቻችሁም ሰላምታ ይገባል፤ መኰንን ከፍ ከፍ የሚያደርገውን ንጉሥ ደጅ እንደሚጸና ከብዙ ቀን ጀምሮ ደጅ መጽናትን ደጅ ጸንቻችኋለሁ፤ ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ሆይ! ጐብኙኝ ቸር ዋልህ ቸር አደርህም በሉኝ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፮. ሰላም እብል ለዘዚኣክሙ ከናፍር፤ ለአፉክሙኒ ሙኀዘ ቅዳሴ መዓር፤ ኢትመንኑኒ አእላፍ ማኅበራኒሁ ለኄር፤ ተዘኪረክሙ እንበለ አበሳ ወነውር፤ ዘበእንቲኣየ ሞተ ወልደ አብ ፍቁር፡፡ | 6. ለዘዚኣክሙ ከናፍር፡- ለእናንተ ከንፈሮች ሰላም እላለሁ፤ የምስጋና መዓርን ለሚያፈሱ አፉችሁ ሰላም እላለሁ፤ የቸሩ ማኅበርተኞች ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ሆይ! ያለ በደልና ያለ ነውር የተወደደ የአብ ልጁ ስለ እኔ እንደሞተ አስባችሁ እኔን አትናቁኝ፡፡ |
| ፯. ሰላም ለአስናኒክሙ ንዋያተ ትፍሥሕት ወኀሤት፤ ለልሳንክሙኒ ነባቤ መለኮት፤ በበዖታክሙ ንዑ አእላፈ አእላፋት፤ ኪያነ ለባርኮ በዛቲ ዕለት፤ ከመ ባረኮ አብርሃም ለይሥሐቅ መሥዋዕት፡፡ | 7. ለአስናኒክሙ፡- የፍጹም ተድላ ደስታ ገንዘቦች ለሆኑ ጥርሶቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ነባቤ መለኮት ለሆነው አንደበታችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ቅዱሳን አእላፈ አእላፋት ሆይ! አብርሃም ይሥሐቅ መሥዋዕትን እንደባረከው በዚኽች ዕለት እኛን ለመባረክ በየወገን በየወገናችሁ ኑ፡፡ |
| ፰. ሰላም ለቃልክሙ ግሩም ወመደንግፅ፤ ለእስትንፋስክሙኒ መዐዛ ጽጌሃ ለዕፅ፤ ዘአልብክሙ ቅያሜ አእላፍ አብያጽ፤ አንትሙ ምስማክየ ወሠዋቅየ እምዳኅፅ፤ ቅድመ ገጽክሙ እሰግድ በገጽ፡፡ | 8. ለቃልክሙ፡- ለሚያስፈራና ለሚያስደነግጥ ቃላችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የዕንጨት የአበባዋ መዐዛ ለሆነው እስትንፋሳችሁም ሰላምታ ይገባል፤ መቀየም የሌለባችሁ ወንድሞች ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! ከዳኅፅ መጠጊያየ እና መደገፊያየ እናንተ ናችሁ፤ በእናንተ ፊት በግንባሬ እሰግዳለሁ፡፡ |
| ፱. ሰላም ለጕርዔክሙ ፈልፈለ ስብሐት ማይ፤ ለክሣድክሙኒ አምሳለ ቢረሌ ጽሩይ፤ ኪያየ ኅድፉ መላእክተ ሰማይ፤ በሐመር ሥልጣንክሙ ከመ ሐመረ ኖኅ ዐባይ፤ ፍጹመ ኢየኀጠኒ ገሃነም ቀላይ፡፡ | 9. ለጕርዔክሙ፡- የምስጋና ውኃ መመንጫ ለሆነው ጕሮሮአችሁ ሰላምታ ይገባል፤ እንደ ብርሌ ለጠራ አንገታችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ቅዱሳን የሰማይ መላእክት ሆይ! ቀላዩ ገሃነም ፈጽሞ እንዳይውጠኝ ከፍ እንዳለች እንደ ኖኅ መርከብ በሥልጣን መርከባችሁ እኔን አሻግሩኝ፡፡ |
| ፲. ሰላም ለመታክፍቲክሙ እለ ይፀውሩ ዘልፈ፤ ለቤዛ አባግዕ ክርስቶስ እምዓባግዒሁ ግዱፈ፤ አእዋመ ሊባኖስ አእላፍ ዘታጼልሉ አእላፈ፤ ጊዜ ድካምየ ኩኑኒ ምዕራፈ፤ ወሶበ ለገይሥ ተንሣእኩ ጸግዉኒ ክንፈ፡፡ | 10. ለመታክፍቲክሙ፡- ከበጎች ቤዛ ከክርስቶስ በጎች የጠፋውን ዘወትር ለሚሸከሙ ትከሻዎቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ብዙዎችን የምታስጠልሉ የሊባኖስ ዛፎች ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! በድካሜ ጊዜ ማረፊያ ለመሔድም በተሣሁ ጊዜ ክንፍን ስጡኝ፡፡ |
| ፲፩. ሰላም ለአክናፊክሙ ዘተደለዉ ለሐዊር፤ ለዘባንክሙኒ እሳታዊ መንበር፤ አመ በእግረ ነፍስ አዐርግ ውስተ ሰማያዊት ሀገር፤ አዝማደ ነፍስየ አእላፍ ተወከፉኒ | 11. ለአክናፊክሙ፡- ለመብረር ለተዘጋጁ ክንፎቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ እሳታዊ መንበር ለሆነው ጀርባችሁም ሰላምታ ይገባል፤ የነፍሴ ወገኖች ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! በነፍስ እግር ወደ ሰማያዊት ሀገር በማርግ ጊዜ በፍቅር |

| | |
|---|---|
| በፍቅር፤ ወኢትትኀየዩኒ እኩን ስላቀ ለፀር፡፡ | ተቀበሉኝ፣ ለጠላትም መዘባበቻ እሆን ዘንድ ችላ አትበሉኝ፡፡ |
| ፲፪. ሰላም ለእንግድዓክሙ መዝገበ ጥበብ ወርቅ፤ ለሕፅንክሙኒ ምርፋቀ ኅሩያን ደቂቅ፤ ዕሩቃነ ሥጋ አእላፍ ዘልብስክሙ መብረቅ፤ ግበሩ ሰላመ ማእከሌየ ወማእከለ አምላክ ጻድቅ፤ እስመ ነገረ ጽልእ ኵሉ የኀልቅ በዕርቅ፡፡ | 12. ለእንግድዓክሙ፡- የጥበብ ወርቅ ሣጥን ለሆነው ደረታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ለተመረጡ ልጆች መጠጊያ ለሆነው ጭናችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ልብሳችሁ መብረቅ የሆነ ከሥጋ የተራቆታችሁ ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! የጥል ነገር ኹሉ በዕርቅ ያልቃልና በእኔ እና በእውነተኛው አምላክ መካከል ሰላምን አድርጉ፡፡ |
| ፲፫. ሰላም ለአእዳዊክሙ እኀዛነ በሊሕ ሰይፍ፤ ወለመዝራዕትክሙ ጽኑዕ እመዝራዕተ ሙሴ ሐዳፍ፤ እምጽንፍ እስከ ጽንፍ ዘትሠርሩ አእላፍ፤ ለባዕል ውስተ ዴዴሁ ከመ አልአዛር ግዱፍ፤ ፍርፋረ ክብርክሙ እብላዕ ሰዱኒ በክንፍ፡፡ | 13. ለአእዳዊክሙ፡- የተሳለ ሰይፍን ለያዙ እጆቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ከአሻጋሪው ሙሴ መዳፍ ይልቅ ለበረታ መዳፋችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የምትበሩ ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! ከባለ ጸጋው በር አልዓዛር እንደወደቀ የክብራችሁን ፍርፋሪ እመገብ ዘንድ በክንፋችሁ ውሰዱኝ፡፡ |
| ፲፬. ሰላም ለኮርናዕክሙ በትረ መዓት ዘኢኮነ፤ ለእመትክሙኒ ዘሐብለ ረድኤት መጠነ፤ ልብሰ ተዋርዶ መሬተ እስመ ተከደንኩ አነ፤ ክቡራን አእላፍ ዘለበስክሙ ብርሃነ፤ መጥዉኒ ልብሰ ክብር ዘየሀይድ ዐይነ፡፡ | 14. ለኮርናዕክሙ፡- የመዓት ብትር ለአልሆነው ክርናችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የመርዳት ገመድን ለለካ ክንዳችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ብርሃንን የተጐናጸፋችሁ ክቡራን አእላፍ ሆይ! እኔ የመዋረድ ልብስ መሬትን ለብሻለሁና ዐይንን የሚያማልል የክብር ልብስን ስጡኝ፡፡ |
| ፲፭. ሰላም ለእራኅክሙ ዘፀበጠ ነበልባለ፤ ከመ በመጽሐፍ ተብህለ፤ ተጋቢአክሙ አእላፍ እለ ቀነትክሙ ኀይለ፤ ሰአልዎ ለሊቅክሙ ዘወይነ ርኅራኄ ተከለ፤ እንበለ ጊዜ ኢይግዝም ኪየየ አስካለ፡፡ | 15. ለእራኅክሙ፡- በመጽሐፍ እንደተነገረ ነበልባልን ለጨበጠ መሐል እጃችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ኀይልን የታጠቃችሁ ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! ፍሬ እኔን ያለጊዜው እንዳይቆርጥ የርኅራኄ ወይንን የተከለ አለቃችሁን ተሰብሰባችሁ ለምኑት፡፡ |
| ፲፮. ሰላም ለአጻብዒክሙ አጻብዐ ክልኤ አእዳው፤ ወለአጽፋሪሆን አኃው፤ መገብተ ቤቱ አእላፍ ለእግዚአብሔር ሕያው፤ መዐዱኒ ወገሥፁኒ ከመ የዋሃን አበው፤ ገሥፆተ ውሉድ ለአብ አኮኑ መፍትው፡፡ | 16. ለአጻብዒክሙ፡- ለወንድሞቻቸው ጥፍሮቻቸውና የኹለት እጆች ጣቶች ለሆኑ ጣቶቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የሕያው እግዚአብሔር የቤቱ መጋቢዎች ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! እንደ ደጋግ አባቶች ምከሩኝ፤ ገሥፁኝም፤ ልጆችን መገሠፅ ለአባቶች የሚገባ ነውና፡፡ |
| ፲፯. ሰላም ለገበዋቲክሙ ሠርጐ ወርቅ ዘኢለብሳ፤ ወለከርሥክሙ ርኁብ እመብልዐ ዕልው ኀሠሣ፤ ካህናተ ሰማይ | 17. ለገበዋቲክሙ፡- የወርቅ ጌጥን ለለበሱ ወገቦቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ከጥፋት ምግብ ፍለጋ ለተራበ ሆዳችሁም ሰላምታ ይገባል፤ የሰማይ ካህናት አእላፍ ሆይ! |

| | |
|---|---|
| አእላፍ አንጽሑኒ እምአበሳ፤ ወዘልፈ ተኖለዉኒ ኢይምሥጠኒ አንበሳ፤ ከመ ዘሥጋ ወደም ወየዋህ እንስሳ፡፡ | ከበደል አንጹኝ፤ እንደ ሥጋ እና ደም እንደ የዋህም እንስሳ አንበሳ እንዳይነጥቀኝ ዘወትር ጠብቁኝ፡፡ |
| ፲፰. ሰላም እብል ለባሕረ ጥበባት ልብክሙ፤ ለኵልያቲክሙኒ እለ ተፈትኑ ቀዲሙ፤ አሠርግዉኒ አእላፍ በንጽሕ ሥርጋዌክሙ፤ ድልወ እኩን ለእግዚእየ ዘመልዕልተ መስቀል ሕማሙ፤ ለነሢአ ቅዱስ ሥጋሁ ወክቡር ደሙ፡፡ | 18. ልብክሙ፡- የጥበባት ባሕር ለሆነው ልባችሁ ሰላምታ ይገባል እላለሁ፤ አስቀድመው ለተፈተኑ ኵላሊቶቻችሁም ሰላምታ ይገባል፤ መከራው በመስቀል ላይ ለሆነው ጌታዬ ቅዱስ ሥጋውን እና ክቡር ደሙን ለመቀበል የበቃሁ እሆን አንድ ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! በንጽሕና ጌጣችሁ አስጊጡኝ፡፡ |
| ፲፱. ሰላም ለኀሊናክሙ ንጹሐ እከያት ኀሊና፤ ለአማዑቲክሙኒ ምስለ ንዋየ ውሥጥ በዕሪና፤ ዝናማተ ክረምት አእላፍ እለ ትጼዐኑ ደመና፤ አቍርሩ ዋዕየ መርቄ ለልቡናየ ኀዘና፤ እስመ አምሰላ ስክርተ ለነፍስየ ሐና፡፡ | 19. ለኀሊናክሙ፡- ከክፉ ኀሊና ለነጻ ኀሊናችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ከውስጥ አካላችሁ ጋርም በእኩልነት ለአንጀታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ በደመና የምትጫኑ የክረምት ዝናቦች ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! የልቡናዬን ኀዘን በረሐ ቃጠሎውን አቀዝቅዙ፣ የነፍሴ ሐና ስካርን አምሳል ሁናለችና፡፡ |
| ፳. ሰላም ለኀንብርትክሙ ማእከለ ጠባይዕ ንብረቱ፤ ለሐቌክሙኒ ዘቀኒተ መክፈ ጥንተ ሥርዐቱ፤ ንጉሠ ዕሥራኤል ዳዊት ከመ ነገረ በትንቢቱ፤ ተአምኖተ ሰብእ መዋቲ አምጣነ ከንቱ ውእቱ፤ ኪያክሙ አእላፍ እምኵሉ እፌቱ፡፡ | 20. ለኀንብርትክሙ፡- አቀማመጡ በጠባይ መካከል ለሆነው እምብርታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ዝናር መታጠቅ ሥርዐቱ ጥንት ለሆነው ወገባችሁም ሰላምታ ይገባል፤ የዕሥራኤል ንጉሥ ዳዊት በትንቢቱ እንደተናገረ የሚሞትን ሰው መታመን ከንቱ ነውና ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! ከኹሉ እናንተን እወዳለሁ፡፡ |
| ፳፩. ሰላም ለአቍያጺክሙ አዕማደ ነፋስ ወነድ፤ ለአብራኪክሙኒ እለ ይትቀነያ በሰጊድ፤ እስመ ኢረከብኩ ኀይለ ለፈጽሞ ኵሉ መፍቅድ፤ አእላፍ ፍቁራንየ ተራድኡኒ በገሀድ፤ ወኢትጸመሙኒ አዕርክትየ ከመ ሰብእ ባዕድ፡፡ | 21. ለአቍያጺክሙ፡- የነፋስና የእሳት ምሰሶዎች ለሆኑ ጭኖቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ በስግደት ለሚገዙ ጕልበቶቻችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ወዳጆቼ ቅዱሳን አእላፍ መላእክት ሆይ! በግልጥ ተራዱኝ፤ ወዳጆቼ እንደ ባዕድ ሰውም ቸል አትበሉኝ፡፡ |
| ፳፪. ሰላም ለአእጋሪክሙ ለሐውዖ ጻድቃነ ወሰማዕት፤ እለ ገይሰ ለመዱ ላዕለ ወታሕተ፤ ነፋሳተ ምሕረት አእላፍ ዘታልሕቁ አዝርእተ፤ ንሥኡኒ እምገጸ ምድር ወአዕርጉኒ መልዕልተ፤ ገጸ አምላኪየ እርአይ እትሜነይ ተምኔተ፡፡ | 22. ለአእጋሪክሙ፡- ጻድቃንን እና ሰማዕታትን ለመጐብኘት ላይና ታች መገሥገሥ ለለመዱ እግሮቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ አዝርዕቶችን የምታሳድጉ የምሕረት ነፋሳት ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! የአምላኬን ፊት አይ ዘንድ ምኞትን እመኛለሁና ከመሬት ፊት አንግሡኝ፤ ወደ ላይም አሳርጉኝ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፳፫. ሰላም ለሰኳንዊክሙ በፍና መስሐቲ እለ ኢሐራ፤ ለመከየድከሙኒ አሣእነ እሳት ዘገብራ፤ ወይነ ቤተ መንግሥት ምሥጢር እለ ትቀድሑ ሐራ፤ አስትዩኒ ጽዋዐ ልብ መጠነ ማእምር ዕዝራ፤ ለቤተ አእምሮ መጽሐፍ ከመ አእምር ግብራ፡፡ | 23. ለሰኳንዊክሙ፡- በስሕተት መንገድ ለአልሔዱ ተረከዞቻችሁ ሰላምታ ይገባል፤ የእሳት ጫማዎችን ለተጫሙ መረገጫዎቻችሁም ሰላምታ ይገባል፤ የቤተ መንግሥት ምሥጢር ወይንን የምትቀዱ ወታደሮች ሆይ! የዕውቀት መጽሐፍ ቤት ግብሯን እንዳውቅ የዕውቀት ሰው የዕዝራን ያህል ጽዋዐ ልቡናን አጠጡኝ፡፡ |
| ፳፬. ሰላም እብል ዘአእጋሪክሙ አጻብዐ፤ ለአጽፋሪክሙኒ ዘዲበ አጻብዕ ተለክዓ፤ ላእካነ መርዓዊ አእላፍ እለ ታስተጋብኡ ሰብአ፤ አብኡኒ ወአንብሩኒ ውስተ ቤተ ሐዲስ መርዓ፤ ከመ ብእሲ ነዳይ ኢይንበር በአፍአ፡፡ | 24. ዘአእጋሪክሙ አጻብዐ፡- ቅዱሳን አእላፍ መላእክት የእግሮቻችሁ ጣቶችን ሰላም እላለሁ፣ በጣቶች ላይ ለተደረደሩ ጥፍሮቻችሁም ሰላምታ ይገባል፤ ሰውን የምትሰበስቡ የሙሽራው መልእክተኞች ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! እንደ ችግረኛ ሰው እዳሪ እንዳልቀመጥ ከአዲሱ ሙሽራ ቤት አስገብታችሁ አስቀምጡኝ፡፡ |
| ፳፭. ሰላም ለቆምክሙ ዘተለዐለ መጠኑ፤ ወለመልክዕክሙ ጽጌ ዘይኤድም ሥኑ፤ እስመ ለሚካኤል ክቡር ለእግዚአብሔር ካህኑ፤ ትነግር ሠናያቲሁ ወዕበያቲሁ ትዜኑ፤ አእላፊ አእላፋት ዑድዋ ለዛቲ መካኑ፡፡ | 25. ለቆምክሙ፡- መጠኑ ከፍ ከፍ ለአለ ቁመታችሁ ሰላምታ ይገባል፤ ውበቱ ለሚያምር አበባ መልካችሁም ሰላምታ ይገባል፤ የእግዚአብሔር አገልጋይ የካህኑ ሚካኤልን በጐነቱን እና ልዕልናውን ትናገራለችና አእላፈ አእላፋት ሆይ! ይኽችን ቦታ ክበቧት፡፡ |
| ፳፮. ኦ አእላፍ ለዘበኀቡዕ ጸለየ፤ ዘትሁብዎ ክሡተ ዕሤተ ጸሎቱ ሠናየ፤ እምታሕተ መሐሪ አምላክ አንትሙ አጋዕዝትየ፤ ዘአቅረብኩ ገብርክሙ ንዋየ ማሕሌት ኅሩየ፤ ተወኪፈክሙ ባርኩ ኪያየ፡፡ | 26. ኦ አእላፍ፡- በሥውር ለጸለየ የጸሎቱን መልካም ዋጋ በግልጥ የምትሰጡ ቅዱሳን አእላፍ ሆይ! ከይቅር ባይ አምላክ በታች ጌቶች እናንተ ናችሁ፤ አገልጋያችሁ የአቀረብሁትን የተመረጠ የምስጋና ገንዘብ ተቀብላችሁ እኔን ባርኩኝ፡፡ |
| ኦ አምላከ አእላፍ መላእክት ዕቀበነ ወድኅነነ ለ..... ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡ | አቤቱ የቅዱሳን አእላፍ መላእክት አምላክ ሆይ! እኛን ባሪያዎችን..... ጠብቀን አድነንም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ |
| አቡነ ዘበሰማያት… | አባታችን ሆይ… |
| ✞ ✞ ✞ | ✞ ✞ ✞ |